# አረ ያገር ያለህ?

የዚያች አገር ዜጎች ከንዋታ
ያለቅሳሉ መንታ መንታ
ምን ሆነው ይሆን? ብሎ
ማየት ለቻለ አስተውሎ
መንታ መንታ በሚያነባው ኃል
በእንባው ሾር ቂም አብቅልዋል።

**                 **                 **

በአፍንጫ ተረተር ተክልለው
ከቅንድብ ስር ተተክለው
ጎን ለጎን እየኖሩ
አይኖቻችን ለጉድ ነው
ሳይቃቃሩ ሳይጣሉ
ጠበኞች እስኪመስሉ
እርስ-በርሳቸው ሳይተያዩ ይኖራሉ።

**                 **                 **

እንደ አርስጣጢለስ ሲናገሩ
በስማቸው የታፈሩ
ግን እንደ ሶቅራጥስ
የተናገሩትን የማይሆኑ
በትግሉ ጎራ የገነኑ
በኑባቤ የነቁ
ከኃድ ሌኒን የላቁ
የዲሞክራሲ ጠበቃዎች
ብዙ አፍርተናል ስታሊኖች።

**                 **                 **

ኩርዝ ለኩሶ በጸሃይ
እንደ ዲዎጋን ባደባባይ
ሰው ሲፈልግ የሰው -ደጋጋ
ከቆላ እስከ ደጋ
ከከተማ እስከ ገጠር
ከመሃይም እስከ ምሁር
በዝምታው ነጋሪት-አስተኔ
አረ የሰው ያለህ? ሲል ወገኔ

በአዳኞቹ ተከብቦ
ጸጥታው ያስፈራል
የዝምታው መስተጋቦ።

** ** **

የስርአቱ ውጋት ፋኖ
የነጻነት ሸማ ጃኖ
የፍትህ ሚዛን የእኩልነት አለኝታ
የቅኔ መምህር የኔታ
ባገር ፍቅር ልቡ የደማ
የለውጥ መርሁ ካስማ
የጨለማ መቅረዝ-ታጋይ
ያ ደብተራ! ኮከብ ሰማይ
ወርዶ ወደ መቃብር - ተከተተ
ብለን አንመን- አበበ እንጅ መቼ ሞተ?

** ** **

ህደጋ ኦጅሎ ህንፍሬ ዋቅጅራ
ህሊማ በለጠች ኦባንግ ወይ አበራ
ጎይቶም ወይ አራርሶ ሁሴንና ሃይሌ
የኦሞ የባሮ የአዋሽ የገናሌ
የአባይ የተከዜ የዋቢ ሸበሌ
ያንድ ወንዝ ልጆች-የጨው ዘር አሞሌ
ይህ ሄደ ያ መጣ- ለአምባገነን ቀንበር
ለምን በሞት ምባድ ይታመሳል አገር?

ጥቅምት 2003

abraham beyenne